# የገላቲያ ጥናት

**የጥናት ክፍል፡ ገላቲያ ምዕራፍ 2**

| መመልከት | መተርጎም | ማዛመድ |
|---|---|---|
| ምን አያለሁ? | ምን ማለቱ ነው? | እንዴት ሊተገበር ይቻላል? |

**ርዕስ፡ እየሞቱ መኖር**

በዚህ ክፍል ውስጥ የተገለጡ ገፀባህሪያትና ከእነርሱ ጋር ተያይዞ የተነገረውን ሀሳብ ተመልከቱ፡፡ ለምሳሌ፡ ጳውሎስ በርናባስን ምን አለ በርናባስ ምን እንዳደረገ ተመልከቱ፡፡

| የእኔ መሞት እና ለርሱ መኖር | የክርስቶስ መሞትና በኔ መኖር |
|---|---|
| ስለ እኔ | በከንቱ ሞተ |
| ሕያው ሆኜ እኖር ዘንድ | ራሱን ሰጠ |
| ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ | ተሰቀለ |
| በሥጋ የምኖርበት ኑሮ | ራሱን ሰጠ |
| ተሰቅዬአለሁ፤ | ወደደኝ |
| በሥጋ እኖራለሁ | በኔ ይኖራል |
| አልኖርም | |

**የመወያያ ጥያቄዎች፡-**



1. በከንቱ መሮጥ ምንድር ነው ጳውሎስ እንዴት ፈተሸው?
2. በክርስቶስ ያለን አርነት ምን ይመስላል?
3. ለእኔና ለበርናባስ ቀኝ እጃቸውን ሰጡን ሲል ምን ማለቱ ነው ቁ.9
4. በበርናባስ በአይሁዶችና በኬፋ ዘንድ የነበረው ግብዝነት ምን ይመስል ነበር?
5. በቁጥር 18 ላይ የፈረሱተንና የሚታነፁትን ነገሮች በክፍሉ መሰረት ዘርዝሩ፡፡
6. መስቀልን ስታዩ ምንደር ነው? ፈጥኖ ወደ አእምሮአችሁ የሚመጣው?
7. የወንጌል እውነት ምድር ነው? እንዴትስ በሰው ፀንቶ ይኖራል?

**ከግል ሕይወት ጋር ማዛመድ እና መተግበር (Application)**

አሁን በስጋ የምንኖርበት ኑሮ ምን ይመስላል? በዛሬው ጥናት መንፈስ ቅዱስ ምን ሰአስተማረኝ? የኔ ድርሻ መንድር ነው?........ በዚህ ሳምንት ምን ላድርግ?

ቀጥሎ ያለውን ቃል በቃላችሁ ያዙና ተናገሩ፡፡

***ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው።***